# ኢሕአፓን አንድ የሚያደርግ ኰሚቴ ተቋቋመ

## መስከረም ፳፪ ፪ሺ፯ ዓ.ም

በ1966 ዓ.ም በኢትዮጵያ ውስጥ የፈነዳውን ሕዝባዊ ማዕበል ተከትሎ ይፋ ከወጡትና ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱት የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ዋነኛው ነው ማለት ይቻላል። በኢሕአፓ ድርጅታዊ ጥላ ሥር ተሰልፈው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት፤ ለአገር ሉዕላዊነትና ሕብረተሰባዊ ዕድገት ሲሉ የህይወት፤ የአካልና የሥነ-ልቦና መስዋዕትነት የከፈሉ አባሎቹ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ናቸው። ዛሬም በድርጅቱ ውስጥ ትግሉን የቀጠሉና በተለያየ ምክንያት ከድርጅቱ ወጥተው በተናጠል የአገራቸውና የሕዝባቸው ችግር እንደ እግር እሳት የሚያንገበግባቸው ወገኖች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው።

በዚህ ድርጅት ወስጥ ያለፍን ሁሉ በወጣት ዕድሚያችን ይዘነው የተነሳነው ሕዝባዊ ጥያቄ እስከ ዛሬ ድረስ መልስ አላገኘም። የአገራችንም ህልውና ከማናቸውም ጊዜ በከፋ አደጋ ላይ ይገኛል። በኢህአፓ ውስጥ ትግላቸውን የቀጠሉ አባላት ይህን እየከፋ የመጣውን የህዝባችንንና የአገራችን ሁኔታ አስተማማኝ መፍትሔ ለማምጣት የሚቻለው በኢህአፓ አመራር ውስጥ እያደገ የመጣው የተክለ ሰውነት ቡቃያ ያሳሰባቸው አባላት ግልጽነትና ተጠያቂነት፤ እንዲሁም የውስጥ ዴሞክራሲ ተግባራዊ በሚሆንበትን መንገድ ሁኔታዎችን ለአባላት አመቻችቶ በትግሉ ውስጥ ያልተካተቱቱን አካቶ ድርጅታችን ሲነሳ ይዞ የተነሳቸውን መተክሎች ይበልጥ አጠናክሮአ ከመታገል ውጭ ሌላ አማራጭ የለለ መሆኑን አስረግጠው፣ ውስጠ ፓርቲ ትግል አደረጉ። በዚህም ምክንያንት ለለውጥና ለግልጽነት ዝግጁ ካልሆኑት የአመራር ቡድኖች ጋር አብሮ መቀጠል አልተቻለም። ስለሆነም ድርጅቱ ከሁለት ተከፈለ። ይህ ክፍፍል የኢትዮጵያን ሕዝብ በጣም ያሳዘነና የብዞዎችን የትግል ሞራል የነካ ነው። አባላቱንና ደጋፊዎችንም እጅግ ያስቆጣ ክስተት ነው። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን ለውጥንና ተጠያቂነትን እንደ ትልቅ ጠላት ከሚፈራው የኢህአፓ ቡድን ውስጥ በርካታ አባላት ከዚህ ቀደም ተነስተው የነበሩትን የውስጥ የዴሞክራሲና የግልጽነት ጥያቄ ይዘው ከፍተኛ ትግል አደርገው አብዛኛው አባላት የእርምት እንቅስቃሴ በሚል መጠሪያ እራሳቸውን ይፋ አደረጉ። በዚህ ጊዜን ነው ኢህአፓን አንድ ለማድረግ መነጋገሪያ እድል የከፈተው። እንደገና ዞሮ ለመገናኜት ጥሩ ሁኔታ የተፈጠረው።

ይኸውም በኢህአፓ ዴሞክራሲያዊ ውስጥ የተጠቃለሉት አባላትና የእርምት እንቅስቃሲ አካላት ይዘውት የተነሱት የውስጥ ዴሞክራሲ፤ የግልጽነትና የተጠያቂነት ጥያቄ ተመሳሳይ ሆኖ በመገኘቱ መቀራረብና መነጋገር ተጀመረ። ከድርጅቶ እርቀው የቆዩትን አባላትም ማሰባሰብና አንድ ሆኖ መታገል የሚሉ ሐሳቦች ተንሸራሸሩ። በተደጋጋሚ በተደረገው ውይይት ኢህአፓን አንድ አድርጎ መቀጠል እንደ ሚቻል ስምምነት

ተደረሰ። ሆኖም ግን ከዚህ በፊት ድርጅቱን በልዩ ልዩ ምክንያት እርቀው የነበሩትን አባሎች ለማሰባሰብ ከመሞከራችን በፊት እኛ በትግል ላይ የቀጥልነው መጀመሪያ አንድ ማሰሪያ ላይ መድረስ አለብን፤ የኢህአፓ አላማ አንድ ነው፤ ይኸውም ለሕዝባችን የዴሞክራሲያዊ መብት፤ ለአገራችን ሉዋዕላዊነት የሚደረግ ትግል ነው። ነገር ግን ይህ ሂደት ወደ ሚቀጥለው ደረጃ  ከፍ ከማለቱ በፊት <u>አሁንም በእያሱ</u> **<u>አለማየሁ</u>** ከሚመራዉ ቡድን ውስጥ የቀሩ አባሎችም ይህንን የተቀደሰ ዓላማ አብረውን መቀጠል እንዲችሉ ሺማግሌ መላክ ያስፈፍልጋል በማለት የኢህአፓ ዴሞክራሲያዊ አቀራራቢ ኮሚቴና የእርምት እንቅስቃሴው ተወካዮች ስምምነት ላይ ደረሱ። በዚህ ስምምነት መሰረት ሺማግሌዎችን በጋራ መርጠው ላኩ። ሺማግሌዎችም የተሰጣቸውን ሐላፍነት በሙሉ ልብ ተቀብለው ሥራቸውን ጀመሩ። ቀነቀጠሮ ወስደው እያሱ ከሚመራው ቡድን ወኪሎች ጋር ተደጋጋሚ ውይይት አደረጉ ሆኖም ግን ከእነ አቶ እያሱ በኩል መዋሃድንና የኢሕአፓ አንድ ሆኖ መቀጠልን የማይፈልጉ መሆኑን ለሽማግሎች አሳወቁ።  በዚህ መሠረት ኢህአፓ ዴሞክራሲያዊና የእርምት እቅንቅስቃሴ አካል በአንድ ላይ ለመታገልና ኢህአፓን ወደ አንድ ጠንካራ ሃይል የማምጣቱን ሥራ ተስማምተን የጀመርን መሆኑ ስንገልጽ በታላቅ ደስታ ነው። ይህም ኢህአፓን አንድ የማድረግ ሥራ በእኛ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ደረጃ በደረጃ በዚህ ትግል ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉና ፍላጎት ያላቸውን ያዚያ ትውልድ ቅርሶች ሁሉ አካቶ ለመሄድ የሚደረግ ሂደት ነው። በቅርብ ጊዜ ኢህአፓ አንድ አድርጎ መሄድ ስለሚቻልበት አቅጣጫና ሂደት መመካከር የሚቻልበትን መድረከም እንደምናዘጋጅ ከወዲሁ እናሳውቃለን።  ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ የኢህአፓን አንድ መሆንና ተጠናክሮ ሲመሰረት ጀምሮ ይዞ የተነሳውን ራዕይ እውን እንዲሆን የምትፈልጉ ሁሉ ትብብራችሁ እንዳይለየን ለማሳሰብ እንወዳለን።

**<u>የ</u>ጋራ ኮሚቴ**

taskforce@gmail.com